ማንነታችን በአደዋ

ታጠቅ መንጂ (22 March 2015)

የማንነት ውድድር - ምክንያቶች ምንድናቸው ? መቼ ተጅመረ ?እንዴት ተጅመረ ? ስንት አይነት ማንነቶች አሉ ? የሰው ልጅ ብቻ ነውን ለማንነት የሚወዳደረ ? ወዘተርፈ የተሰኙትን ጥያቄዎች መመለሱንና መግለጹን ትቼ ፤ በእኔ እይታ አሁን ያለንበት ዓለም ሁለ-እንተናዊ እድገት- የማንነት ማስመስከርያ ውድድሮች ውጤት (ፕሮዳክት) ነው እላለሁ ። ብሄሮች ፣ አገሮች ፣ አሁጉሮች ፣ግለሰዎች ፣ቡድኖች ወዘተርፈ ለማንነት ይወዳደራሉ ።

- ማንነት በጦር ሜዳ
- ማንነት በመልካም አስተዳደር
- ማንነት - በጥንታዊ አገርነት፣በጥንት ቅርጻ ቅርጽ ፣በጥንታዊ ሥልጣኔ በመታወቅ
- ማንነት - በኢንዱስትሪ ፣ በቴክኖሎጂ ፣ በኮሚኒኬሽን ወዘተርፈ ሥልጣኔ
- ማንነት - በንጥረ ነገሮች (በኬሚስትሪ) ፣ በሃይል ምንጭ (በፊዚክስ)፣ በመደሃኒት ቅመማ ወዘተ.. ጥናትና ምርምር ለኖብል ሽልማት በመብቃት
- ማንነት - በሥነጽሁፍ ፣ በፍልስፍና ፣በማህበራዊ ሳይንስ ፣በኤኮኖሚክስ ሳይንስ ጥናቶች እውቅና በማግኘት
- ማንነት - ዓለምን በማራጋጋትና ሰላም በማስፈን ሥራ - የኖብል ሽልማት በመወሰድ
- ማንነት - በኦለምፒክ በተለያዩ የስፖርት ግጥሚያዎች - የወርቅ ፣ የብርና የነሃስ መዳሊያ በማግኘት
- ከባዕዳን አገዛዝ ነጻ ሆኖ የመኖር ማንነት ፤ ብሄራዊ ሉዓላዊነትን፣ታሪክን፣ ባህልን፣ ቋንቋን፣ እኔነትን ወዘተ..ሣያስደፍሩና ሳያስነኩ በኩራት የመኖር ማንነት። እነዚህን ማንነቶች በቅኝ ገዢዮች ሥር ከወደቁ -የሚኖረው ግንኙነት - የባሬያና የጌታ ነው የሚሆነው

እናንተ ግማሽ ሰው ናችሁ ፣እናንተ ከእኛ በታች ናችሁ ፣እናንተ እኛን ማገልገል አለባችሁ ፣የተፈጥራችሁት በእኛ እንድትገዙ ነው - በማለት በንቀትና በትምክህት ከአውሮፓ ወደ ኢትዮጵያ የገሰገሰውን የጣሊያን

ሠራዊት የካቲት 23 ቀን 1888 አደዋ ላይ በጀግኖች አያቶቻችን ድባቅ ተመታ ። ስለሆነም የማንነቶች ሁሉ ማንነት አጎናጽፈውናል

ለእኛ ብቻ ሳይሆን ነጭን በጥቁር ሰው እንደሚሸነፍ ለሞላው ዓለም ጥቁሮች አስተምረው አልፈዋል ።

“በአደዋ ጦርነት የምኒሊክ ሠራዊት 40%ን የኢጣሊያን ወታደር ገድለዋል ፤ አቆሰለዋል ። ከጦርነቱ በኋላ የፈረንሳይና የእንግሊዝ ሉዕካን ወደ አዲስ አበባ ሄደው አጼ ምኒሊክ በአፍሪካም በአውሮፓም ከወቅቱ ሃያል መንግሥታት አንዱ መሆናቸውን እውቅና ሰጥቷቸው ተመለሱ” በማለት (ሪቻርድ ፓንክረስ) መሰከሯል።

“ኢትዮጵያውያን አርበኞች የማረኩዋቸውን 1800 ኢጣሊያኖች- ስብዕና በተካሃነ ሁኔታ ተስተናግደው -ሁሉንም በሰላም ወደ አገራቸው ተመልሰዋል ፤ ያንን በጎ ሥራ - በምኒሊክና በአውሮፓውያን መካከል መልካም የዲፕሎማሲ ግንኙነት እንዲፈጠር ረቷል” በማለት (አቬዲዝ ቴራዚያን) መስከሯል ።

እ.አ.አ ከ 1888 -1940 የኖረው -የራስተፈሪያን እምነት መሰረት የጣለውና የሞላ ዓለም ጥቁሮች መሻሻል ድረጅት (ዩኒቨርሳል ኔግሮ ኢምፕሩቨሜንት አሶሴሽን) መሪ የነበረው ጃሜካዊው ማርከስ ጋርቪ - ከአደዋ ጦርነት በኋላ ፡-

-ሁሉንም ጥቁሮች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እንዲኮሩ

-ኢትዮጵያ ሁሉንም ጥቁር ነጻ ታወጣለች

-እኛ ጥቁሮች ተሰቃይተናል፣ ወድ ኢትዮጵያ መሄድ አለብን (ባክ ቱ ኢትዮጵያ) ወዘተ.. እያለ ይሰብክና ያስተምር ነብር ።

ነገርግን በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ወቅት ሃይለሥላሴ ሸሽተው ወደ አውሮፓ ሂደዋል የሚል ወሬ በመስማቱ -በሃይለሥላሴ እና በኢትዮጵያ ላይ የነበረው ተስፋና ኩራት ወደ አሉታነት ተለወጠ ። ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ በብስጭትና በህመም ምክንያት በለንድን ከተማ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ

አደዋ

ጠላትሽን ያዋረድሽ

ጠላትሽን የቀበርሽ

እምቢ በባዕድ አልገዛም ያልሽ

ከአጥናፍ እስከ-አጥናፍ የታወቅሽ

ሁሉንም የታርክ ማህደር የመዘገበሽ

ማንነታችን የተመሰከርብሽ

ጅግኖቻችንን ያስመሰከርንብሽ

የጥቁር ሕዝብ የነጻነት ጮራ የፈነጠቀብሽ

የድል እምቢልታ የተነፋብሽ

መኩሬያና መመኪያችን የነበርሽ

አደዋ ዛሬ ምነካሽ

ምነው ስምሽን በከልሽ

ምን በከለው ማህጸንሽ

ምነው አጥፊዮችሽን ወለድሽ?

ምነው የእናት ጡት ቆራጭ ከሃዲዎች አበቀልሽ

ምነው ባንዳዎች ኮተኮትሽ

የጣሊያን ደም በማህጸንሽ ስለቀበርሽ ይሆን?

የጣሊያን አጥንት በከርስሽ በመያዝሽ ይሆን?

እነመለስ ዜናዊ እናቶች በዝያ ላይ የበቀለ እህል በልተው ይሆን?

በዚያ ላይ የሚወርድ ወንዝ ውሃ ጠጥተው ይሆን?

የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ ስነልቦናና በጋራ ክንዱ ወያኔዎችን ያምበረክካል!

ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘላዓለም ይኑሩ !